ቀን ኅዳር ፳፯÷፳፻፮ (27/03/06)ዓ.ም

ለክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለማርያም ደሰለኝ!

ጉዳዩ፡ ከእግዚአብሔር የተገለጹትን መልእክቶች ማስተላለፍ ይሆናል

ሰላሙንና ጤናዉን፣ መልካሙንና ምሕረቱን፣ ትእግስቱንና ጽናቱን፣ ጽድቅና ቅድስናዉን፣ ባጠቃላይ ለምድራዊዉም ሆነ ለሰማያዊዉ መልካሙንና የተቀደሰዉን ሕይወት የምመኝለዎ ክቡር ጠቅላይ ሚስትር ኃይለማርያም! እግዚአብሔር ሁሉ የእርሱ በእርሱ ለእርሱ የሆነ አምላክ እድሜና ጤናዉን ሰቶን ለዚህ ጊዜ እንኳን አበቃን፤ እኔንም መልእክቱን እንዳደርስ እርሶም እንዲደርሶት ፈቃዱ የሆነ አምላክ ዛሬም ዘወትርም ለሕያዉነት ዘመን ስሙ የተመሰገነ ይሁን እያልኩ ወደ ፍሬ ጉዳዩ እገባለሁ::

የእግዚብሔር ጥሪ ደርሶኝ ከመስከረም ፳፻፫ (2003) ዓ.ም ጀምሮ እስከአሁን ድረስ እርሱ በመራኝ መንገድ ሁሉ መልእክቶቹን ለኢትዮጵያዉያንና ለዓለም ሕዝብ እያደረስኩ የምገኝ ሲሆን፤ ቀደም ሲል በመድኃኔዓለም እለት የካቲት፳፯÷፳፻፬ (27/06/2004) ዓ.ም ለቀድሞ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ የመጨረሻ ማስጠንቀቂያና መልእክት እንዳደርስ እንዳደረገ ሁሉ አሁን ደግሞ ዛሬ በመታሰቢያዉ በዚያዉ እለት ለእርሶ እንድጽፍ አድርጓል::

በእኔ በኩል እግዚአብሔር ያስተላለፈዉ ሦስት መልእክቶች ሲሆኑ፤ የመጀመሪያዉ « **የኢትዮጵያና የዓለም የመጨረሻ ፍርድ አፈጻጸም ዉሳኔ**» በሚል ርእስ ከመስከረም፩ (1) እስከ ወሩ ማለቂያ ፳፻፫ (2003) ዓ.ም ድረስ በተለያየ ቀንና ሰዓት ያጻፈኝ 76 ገጽ የያዘ ነዉ:: ሁለተኛዉ ደግሞ ከመስከረም አጋማሽ እስከ ታኅሣሥ አጋማሽ ፳፻፬ (2004)ዓ.ም «**የጨለማዉ ገዥ ተግባርና ንግግር**» በሚል ርእስ የተጻፈዉ 462 ገጽ የያዘ ነዉ:: ሦስተኛዉ መልእክት ደግሞ ከነሐሴ ፲፰÷፳፻፬ (18/12/2004) ዓ.ም ጀመሮ እስከ ኅዳር፲፪÷፳፻፭ (12/03/2005) ዓ.ም «**ታላቅ የብርሃን ተስፋ ለኢትዮጵያዉያንና ለዓለም በሙሉ**» በሚል ርእስ ያጻፈኝ 617 ገጽ የያዘ ነዉ:: ሌሎች በእርሱ አሳሳቢነት የተጻፉ ደብዳቤዎች **የመጀመሪያዉ ለአቶ መለስ ዜናዉ** በየካቲት ፳፯÷፳፻፬ (27/06/2004)ዓ.ም የተጻፈ፤ **ሁለተኛዉ ደግሞ ለተለያዩ መንፈሳዊ ብሎጎች** በሰኔ ፲፭÷፳፻፬ (15/10/2004) ዓ.ም የተጻፈ፤ **ሦስተኛዉ ደግሞ ለኢትዮጵያዉያንና ለዓለም ሕዝብ** በነሐሴ ፩÷፳፻፬ (1/12/2004) ዓ.ም ተጽፎ በነሐሴ፲፭÷ ፳፻፬ (15/12/2004) ዓ.ም የተላለፈ፤ **አራተኛዉ ለሚሽሪያ መጽሔት** ኅዳር፲፪÷ ፳፻፭ (12/03/05) ዓ.ም የተላለፈ፤ **አምስተኛዉ ደግሞ እስከ መቼ ለተባሉ ግለስብ(አካላት)** መጋቢት፳፬÷፳፻፭ (24/07/2005) ዓ.ም የተላለፈ ነዉ:: ይህ ደግሞ ስድስተኛ ነዉ:: እንደ ሦስተኛዉ መልእክት የመጨረሻ ይሁን አይሁን እግዚብሔር ነዉ የሚያዉቀዉ:: ሦስተኛዉ የእግዚአብሔር መልእክት የመጨረሻ እንደሆነ ገምቼ ነበር፤ ይኸዉ እንደግምቴ በየዓመቱ ይመጣ

የነበረዉ ነፍሴ ብቻ የምትሰማዉ ልዩ የእግዚአብሔር ድምፅ በ፳፻፮ (2006) ዓ.ም ለአራተኛ መልእክት ወደ እኔ አልመጣምና::

ስለ እርሶ ገና ጠቅላይ ሚኒስትር ሳይሆኑ በ2004 ዓ.ም በተጻፈዉ ሁለተኛ የእግዚአብሔር መልእክት«የጨለማዉ ገዥ ተግባርና ንግግር» በሚል ርእስ በክፍል ሦስት በምእራፍ አንድ ከገጽ 263-266 ላይ የተጻፈዉን ያስተዋልኩትና ያወኩት በ፳፻፭ (2005) ዓ.ም «ታላቅ የብርሃን ተስፋ ለኢትዮጵያዉንና ለዓለም ሕዝብ» በሚል ርእስ በተጻፈዉ ሦስተኛዉ የእግዚአብሔር መልእክት ወደ ጽሑፉ መጨረሻዉ ማጠናቀቂ ጊዜ ነበር:: በሦስተኛ መልእክት በክፍል ዘጠኝ በምእራፍ ሁለት ከገጽ 509-514 ላይ ያለዉን በማስተዋል ያንብቡት:: አጻጻፉ እግዚአብሔር የሚገልጽለት ሰዉ ብቻ እንዲያዉቀዉና እንዲያስተዉለዉ ተድርጎ ነዉ የተጻፈዉ:: ይህን እግዚአብሔር እንዲገለጽበት የፈቀደዉ አገላለጽ ስለሆነ ነዉ:: እንግዲህ በአገላለጹ ሐሳብ የእርሶ ምድቦት «የዓመፃ ልጆች፣ የዲያብሎስ አገልጋዮች» ተብለዉ ከተገሰጹትና ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነትን እንዲሁም የቅዱሱ ኪዳን ሃይማኖት ለማጥፋት ከተሰለፉ የጥፋት ልጆች ጋር ሳይሆን የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊትንና የቅዱሱ ኪዳን ተዋሕዶ ሃይማኖትን ለማስጠበቅ ከተሰለፉ የቅዱስ ኪዳኗ ኢትዮጵያ ልጆች ጋር ስለሆነ ዛሬ ነገ ሳይሉ ከዓመፃ ልጆችና ከዲያቢሎስ ስራ አስፈጻሚዎች ራሶትን ይለዩ:: እነሱ እጅግ በቅርቡ በእግዚአብሔር ቁጣ የሚጠረጉና መታሰቢያቸዉ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ የሚጠፋ፤ የሚቀራቸዉም የዘሩትን የክፋት፣ የተንኮል፣ የጥላቻና የበቀል፣ የዘረኝነትና የጎጠኝነት፣ አምልኮ ባዕድ፣ ባጠቃላይ የዓመፃ፣ የክህደት፣ የርኩሰት ፍሬያቸዉን መራራ ቢሆንም ጠጥተዉ በምድርም ዋጋ ከፍለዉ ወደ ሁለተኛዉና ወደ መረጡት እንዲሁም ለጌታቸዉ ለጨለማዉ ገዥ ተጋድሎ ወዳደረጉበት ለዘላለም ዋጋ ወደሚከፍለቡት የጨለማ ስፍራ መሄድ ነዉ::

ታዲያ እርሶ ከእነዚህ ከሃዲያንና ዓማፅያን የዲያብሎስ ሥራ አስፈጻሚዎች ጋር ምን አንድነትና ኅብረት አሎት!?:: እነዚህ ቀጣፊዎች በአንደበታቸዉ የሚያወሩት ሌላ፣ በተግባር የሚፈጽሙት ሌላ፣ ዉስጣቸው ጥላቻና በቀል የሞላ፣ ዓመፃና ትዕቢት የሞላባቸዉ፣ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነትን እንዲሁም የቅዱሱ ኪዳን ተዋሕዶ ሃያማኖት ለማጣፋት የሞት ሽረት እያደጉ ያሉ፤ የዓመፃ፣ የክህደት፣ የግፍና የርኩሰት ጽዋቸዉ ሞልቶ እየፈሰሰ ያለ፤ የባለጊዜነታቸዉ ዘመንም በአራት ነጥብ የተደመደመ፣ የሚቀራቸዉም የዘሩትን መራራ ፍሬ ቋቅ እያላዉቸም ቢሆን ጠጥቶ ማለፍ ብቻ ነዉ:: ከዚያ በኋላ ነዉ የኢትዮጵያ ትንሣኤ ለዓለም የሚገለጸዉና በሥጋዊዉም ሆነ በመንፈሳዊዉም ወንበር ላይ እርሱ የቀባቸዉና የመረጣቸዉ ቅኖችና እዉነተኞች እንዲሁም የእመቤታችን ድንግል ማርያም ባለሚሎች ተቀምጠዉ በኢትዮጵያ ብቻ አይደለም በዓለም ላይ በአራቱም ማእዘን ፈቃዱን የሚፈጽሙትና የሚያስፈጽሙት:: እንዲሁም በድህነቷ፣ በጦርነት፣ በችግር፣ በስደት፣ በረሀብ፣ ባጠቃላይ በመከራና በጉስቁልና ሕይወትና ኑሮ የምትታወቀዉ እናት ሀገራችን ቅድስት ኢትዮጵያ ለዓለም በረከትና ብርሃን የምትሆነዉ::

እንግዲህ ምንም እንኳን በሁለተኛ የእግዚአብሔር መልእክት ላይ በተገለጸዉ መሰረት የተወሰነ ፈተናና መከራ ሊያጋጥሞት ቢችልም፤ በሥጋም በነፍስም የሚጠቀሙበት ስለ እዉነት ብቻ ሲመሰክሩና የዲያብሎስ አገልጋዮችን ስዉር የዓመፃ ተግባራቸዉን ሲያጋልጡ ብቻ ስለሆነ፤ ስለ እዉነት ራሶትን ሊክዱና እዉነትን ሊቀበሉ ከዚያም ሊመሰክሩ ይገባል። ምክንያቱም ይህን ካደረጉ በኢትዮጵያ ትንሣኤ ዘመንም ትልቅ አገልግሎት የሚጠብቆትና በሥጋም በነፍስም የሚጠቀሙበት ነዉ።

በመጨረሻም ከላይ በዝርዝር የተገለጹት ሦስት የእግዚአብሔር መልእክቶችና በመንፈስ ቅዱስ አሳሳቢነት የተጻፉ አምስት ደብዳቤዎች እንዲሁም የዓመፃ ተግባርና ልጆች ከኢትዮጵያና ከዓለም ከጸዱ በኋላ በኢትዮጵያ ትንሣኤ ዘመን የእግዚአብሔርን ፈቃድ ብቻ ለመፈጸምና ለማስፈጸም ኢትዮጵያም ሆነች ዓለም ተላልፋ የተሰጠችዉ የእመቤታችን ባለሟልና እንደራሴ የሆኑት «ሣልሳዊ ቴዎድሮስ» በመባል የሚጠበቁት ከኅዳር፯÷፲፱፻፺፰ (7/03/1998) ዓ.ም እስከ መስከረም፳፩÷፳፻፬ (21/1/2004) ዓ.ም ድረስ ለኢትዮጵያዉያንና ለዓለም ሕዝብ ያስተላለፉት የአራት ጊዜ የእግዚአብሔር መልእክታት በአንድ ላይ «ኢትዮጵያ የዓለም ብርሃን» በሚል ርእስ ያስላለፉትን ባጠቃላይ ሁሉንም በአንድ ፎልደር በሲዲ ላይ አድርጌ ከዚህ ደብዳቤ ጋር የላኩሎት ስለሆነ እርሶም ሆኑ በቅንነትና በየዋሕነት እንዲሁም በታማኝነትና በኢትዮጵያዊነት ስሜት ለአገራቸዉና ለሕዝቡ አገልግሎት እየሰጡ ያሉ ጥቂት የሥራ ባልደረባዎቾ አንብባችሁ እንድትጠቀሙበትና የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ተግባራዊ እንድታድርጉ በማክበር አሳስቦታለሁ። እግዚአብሔር አምላክ ከቁጣዉና ከጠረጋዉ ሰዉሮን ለኢትዮጵያ ትንሣኤና ለማያልፈዉ ሰማያዊ መንግሥቱ ያብቃን ይላል ታናሹ ወንድሞት ተክለ ኪዳን።

*ወስብሓት ለእግዚአብሔር ወለወላዲቱ ድንግል ማርያም።*

*አድራሻ* *<teklekidan979@yahoo.com>*

***<u>ግልባጭ</u>***

*♀ለእዉነተኛዉ ለእግዚአብሔርና ለእመቤታችን ድንግል ማርያም ባለሟልና እንደራሴ ካህኑ እጨጌ።*

*♀ለእዉነተኛዉ ለእግዚአብሔርና ለእመቤታችን ድንግል ማርያም ባለሟልና እንደራሴ ካህኑ ርእሰ ነገሥታት።*

*♀ከዚህ በፊት የተለያየ ደብዳቤና የእግዚአብሔር መልእክት ለደረሳችሁና ለሚደርሳችሁ ሁሉ*